PANORAMA #

## <u>የትዝብት አድማስ</u>

*መጋቢት* 21 2000 *ዓም*

## <u>ብሔራዊ አቅጣጫችን ምንድን ነው? ወዴትስ ያመራል?</u>

***ከአስራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድስት ዓም ጀምሮ÷ ሀገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ አጋጥሟት በማያውቅ ከፍተኛ የለውጥ ማዕበልና ብሔራዊ ቀውስ ውስጥ እንደ ቆየች÷ አሁንም በዚሁ ሁኔታ እንደምትገኝ ሁሉም የሚያወቀው ክስተት ነው፡፡ ከ66 ዓም ወዲህ በርካታ የዓለም ሀገሮች የየራሳቸውን ብሔራዊ -ሕዝባዊ አመፅ አድርገዋል፡፡ በሂደታቸውም÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈለውንም ያህል እንኳን ባይሆንም÷ ከባድ መሥዋዕት ከፍለዋል፡፡ ግን ከሞላ ጎደል ዓላማቸውን መትተዋል ለማለት ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት ከፈነዳ ወዲህ ÷በርካታ ሀገሮች የየራሳቸውን አብዮት ማካሄዳቸው ÷ የኅብረተስብ ዕድገትና ሂደት ክስተት በመሆኑ÷ ሊያስገርም ባይችልም÷ የአመፃቸውን ፍሬና ውጤት አግኝተው ወደ ብሔራዊ ዕድገትና የልማት እንቅስቃሴ ሲያመሩ÷ እኛ ግን የዚህ ዕድል ተሳታፊዎች ልንሆን አልበቃንም፡፡ ከእኛ በኋላ÷ ኒካራጓ÷ ደቡብ አፍሪካ÷ ኢራቅ÷ በርካታ የደቡብ አሜሪካ ሀገሮችና ሌሎቹም በዓለም ዙሪያ የሚኖሩ ሕዝቦች በአካሄዱት ሕዝባዊ አመፅ÷ ከፍተኛ ለውጥ በማድረግ የፈለጉትን ከፍተኛ የዕድገት ዕመርታ አስመዝግበዋል፡፡ እኛ ግን በታሪካችን ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ መከራና ዕልቂት ቢደርስብንም÷ አሁንም ገና ልማቱንና ዕድገቱን ማግኘት አልቻልንም፡፡ ልማቱና ዕድገቱ ቀርቶ÷ ሰላምና መረጋጋት እንኳን አላገኘንም፡፡ የሀገራችንም ኅልውና በከፍተኛ አደጋ ላይ እንደሚገኝ የሁሉም ስጋትና ጭንቀት ሆኗል፡፡***

***<u>ሦስተኛውን አምባገነን ሥርዓት ጥለን÷ ሌላ አራተኛ አገዛዝ እንዳይመጣብን የምንሰጋው ዜጎች ቁጥራችን ቀላል አይደለም ብለው የሚያምኑ ዜጎች ቁጥራቸው ይህ ነው አይባልም፡፡</u> አሁን ከተያዘው ሁኔታና ሂደት÷ ከሕዝብ ዕልቂት ከሀገር ጥፋትና ውድመት÷ ለመከላከል የሚያስችለን ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የሚያካትት መሠረተ-ሰፊ አቅጣጫና አመራር የሚስጥ ብሔራዊ መድርክ አልተገኘም፡፡ ከእስራትና ከስደት÷ ከረሀብና ጠኔ÷ ከጅምላ ጭፍጨፋና ግድያ÷ ከጦርነት ስጋት ለመውጣት አልቻልንም፡፡ ዛሬም እንደትላንቱ ዋይታና ለቅሶ÷ ሰቆቃና ቡታ ÷ ስደትና መንከራተት የብሔራዊ ገጽታችን መታወቂያ÷ የዜግነታችንም መለያ እንደ ሆነ ነው፡፡ የዓለም ሕዝቦች መዛበቻና ማሽሟጠጫ÷ የጎረበቶቻችን መሳለቂያ መሆናችንን እንኳ ለመገንዘብ አልቻልንም፡፡ የራሳችንን ችግር እራሳችን መፍታት እየተሳነን÷ ለችግሮቻች ምክንያቶች ሌሎች እንደሆኑ እንቆጥራለን፡፡ እስከ መቸ ድረስ የአምባገነኖች ሥርዓት ሰለባዎች ሆነን እንደምንኖር ለማወቅ ተስኖን÷ መፍተሄ ብለን የያዝነው ይህችን " የማያልፍላትን" ሀገር ጥሎ መሰደድን ነው፡፡ በተፈጥሮ ፀጋዎች የተደለች***

ሀገር ብቻ ሳይሆን፥ ግምቱ በትክክል የማይነገርለት የደለበ ሃብትና ማዕድኑት ያላት ምድር ባለቤቶች መሆናችንን እንኳ ተረድተን ያንን መጠቀም ተስኖን የዓለም ተመፅዋዕቶች ለመሆን ለምን በቃን? የሚለውን ጥያቄ እንኳ ጠይቀን መልሱን ለማወቅ ተጨንቀን አናውቅም:: ይህንን ሁሉ ለማንሳት የተነሳሳነው፥ የጋራ ችግራችንን በጋራ ለመወያየትን የሚበጀውን መፍተሄ ለመወያየት እንድንችል ብለን እንጅ፥ እኛ የሞራል ሥልጣኑ ኖሮን ፥"ከመምሕሩ ደቀ-መዝምሩ" ለሚለው ይትብኃል ለመመቻቸት ፍላጎቱ ኖሮን አይደለም:: ወይም ደግሞ የጨለምተኝነት አባዜ ኖሮንም አይደለም:: በመሠረቱ፥ ጨለምተኝነት የኢትዮጵያዊነት በኅላችን አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን የቆምንለት ዓላማ እንኳ ቢሆን አይፈቅድልንም::

ታዲያ ዕውነቱን ተናግረን ከመሸበት እንደር ማለትን ከተፈቀደልን፥ አሁንም ለብሔራዊ ችግሮቻችን ማስወገጃ የሚሆነን ብሔራዊ መፍተሄ ለመፈለግ የሚያስችለንን በጋራ ብሔራዊ ራዕይ መስማማት ቀርቶ፥የጋራ የትግል አቅጣጫ ለመቀየስ እንኳን ተስኖናል:: እስካሁን! ሌላው ቀርቶ፥ምን ዓይነት ብሔራዊ ዕፀዕ እንደገጠመን እንኳን ደፍረን ለመነጋገር ፥ ማስተዋሉም፥ ትዕግስቱም፥ ትህትናውም፥ቆራጥነቱም ሆነ ግልፅነቱ የለንም:: ሀቀኝነት፥ ታማኝነት፥ተማምኖ ለመከባበር፥ተዋውቆ ለመተባበር፥ ከአድማስ ባሻገር ለማየት፥ ስለብሔራዊ ራዕይ ለማሰብ፥ ከግል ዝና ፥ ከከንቱ ውዳሴና ከግል ድርጅት ጥቅም በላይ ለመመለክት ገና ብዙ ምዕራፍ መሄድ እንዳለብን የተገነዘብነው አንመስልም:: ዘለዓለም ስለ ችግራችንና ድክመታችን እያወራን መኖሩ፥ እስካሁን ምንም መፍተሔ እንዳላስገኘልን ከልብ ተቀብለን በመፍተሔ ፍለጋው ላይ ማተኮር ይገባናል:: <u>የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችለንን ብልኃትና ዘዴ ማግኘት አጣዳፊ ተግባራችን እንጅ በስብሰባ ብቻ የሚገልጽ ነባቢት ሆኖ የሚቀር ጉዳይ አይደለም::</u>

በታሪክ ሂደት ውስጥ የሚፈራረቅ ትውልድ ፥ የራሱን ብሔራዊ ችግር ፈትቶ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ሥራ ሰርቶ ያልፋል እንጅ የራሱን ችግር ለተተኪው ትውልድ አውርሶ አይሄድም:: ብሔራዊ አቅጣጫ ቀይሶ በብሔራዊ ሂደት መጓዝ ከተቻለ፥ በአስተማማኝ ሁኔታ ከብሔራዊ ግብ ለመድረስ ከባድ አይሆንም:: የጋራ አጀንዳን ነድፎ፥ የጋራ ብሔራዊ ዓላማን አንግቦ፥ ብሔራዊ ግብን ለመምታት ያነጣጠረ ትግል፥ በአቸናፊነት እንደሚጠናቀቅ በርካታ የታሪክ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል::

ምናልባት በዚህ ሀቅ መስማማት ከተቻለ፥ ለምን ብሔራዊ አቅጣጫው ጠፋብን? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ በተገቢ መልኩ መልስን፥ አቅጫችንን እንዳንቀይስ ደንቃራ ከሆኑብን ብዙ እንቅፋቶች አንዱ፥ ከራሳችን ጋር ታርቀን ከሌሎቹ ጋር ለመታረቅ ፈቃደኞችና ዝግጁዎች አለመሆናችን እንደሆነ ይታመናል:: ታዲያ ይህ ደግሞ በበኩሉ፥ ጠላቶቻችን "ሀበሾች፥ እንኳን ተስማምተው በጋራ ሊሰሩ ቀርቶ፥ ላለመስማማትም ቢሆን የሚስማሙ ፍጥረቶች አይደሉም" የሚለውን "ጠላት ይቀባል ጠላት" ዓይነት ዝባንዝንኪ ተረት ተረት ዝም ብሎ መስማት፥ ማጠየቂያ እንደመስጠት

ይሆናል። ይህን የሚቀበሉ ካሉ ተሳስተዋል። ምክንያቱም በዘመናት ኢትዮጵያውያን-ያት ተስማምተው በጋራ ሀገራቸውን በነፃነት እስካሁን ድረስ አቆይተዋልና!

ከዘህም በቀር እኛ በበኩላችን የምናምነው ፦

- የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ በዘመናት በጋራ ተስማምቶ፥ ተባብሮ፥ ሀገሩን በነፃነት ጠብቆ በማቆየት ለዚህ ለዛሬው አሳረኛ ትውልድ፥ ማስረከቡን፥

- ገዥዎቹ ከሚያመጡት የየግላቸው ጦርነትና ውጊያ በስተቀር፥ የኢትዮጵያውያ ሕዝብ፥ በብሔርም ይሁን በጎሳ፥ በዘርም ሆነ በቋንቋ፥ በኃይማኖትም ይሁን በክልል የተጋጨበት አጋጣሚ ታሪክ መመዝገቡን አለማወቃችንን፥

- ሴቶች ፥ በጥጥ ደቦ፥ ወንዶች፥ በእርሻ ወበራ፥ በማሕበራዊ፥ በኢኮኖሚ ባኅላዊና ኃይማኖታዊ ትስስር አብሮው የኖሩ መሆናቸውንና፥ የጋራ ችግራቸውን በጋራ የመፍታት ልማዳቸው መሆኑን የምናውቅው መሆናችንን፥

- ይህ የሕዝብ ታሪካዊ፥ ማኅበረሰባዊ፥ ባኅላዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ደግሞ በበኩሉ፥ ብሔራዊ አቅጣጫንና ራዕይን በማገናዘብ አብሮ ተስማምቶና ተከባብሮ ለመኖር አብቅቷቸዋል። የዚህ ሁሉ መሠረቱና ምሶሶው ደግሞ የኢትዮጵያዊ ዓብነትና ምሥጢራቸው ነበር። የጋራ ጠላታቸውን ጥቃት ለመከላከል ወደ ጦር ሜዳ ሲሄዱም፥ "ምሥጢርክን በጉያ ስንቅህን በአህያ" የሚለውን ሀገራዊ መፈክርን በማንገብ ነበር። ይህ የኢትዮጵያዊ ዓብነትና ማንነት መቀጠል አለበት ብለን እናምናለን። የማይቀጥለበት ምክንያት ደግሞ ጭራሽ አይታየንም።

" ሁሉም መንገዶች ወደ ሮም ያመራሉ" እንደሚባለው፥ እኛም ሁለንተናዊ አቅማችን፥ ትኩረታችን፥ ኃይላችን፥ አእምሯችንና ዓላማችንን <u>ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲያመሩ ማድረግ፥ የወቅቱ መፈክርና የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀዳማይ ጥያቄ ሆኗል።</u> ይህንን አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄ በመሠረታዊ መልኩ መመለስ ከተቻለ ደግሞ፥ ብሔራዊ አቅጣጫን የቀየሰ ትግል ምን ዓይነት ስልትና ስትራተጅ መያዝ አለበት? የሚለውን ዐበይት ጉዳይ ማንሳት ሊኖርብን ነው።

በእኛ ዕምነት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የማነኛውም ጉዳይ ሁሉ ባለቤትና አዛዥ፥ አድራጊ-ፈጣሪ፥ ወሳኝና ፈራጅ፥ ነው እንላለን። ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ በመሆኑም፥ የህግ የበላይነትንም ይሁን፥ የራሱንና የሀገሩን ልዕዋላዊነት

አስከብሮና ጠብቆ፥ በነፃነት፥ በሰላምና በብልፅግና መኖር የሚችል ሕዝብ ነው ብለንም እናምናለን፡፡ የሰላም ጌታና የጦርነትም አስወጋጅ በመሆኑ፥ መለስና ተባባሪዎቹ የሠላሙን በር ሁሉ ቢዘጉበትም፥ የሰላም ባለቤት በመሆኑ፥ ጦርነትና ውድመት እንዳይመጣና በሀገሩ ላይ እልቂት እንዳይደረግ የመከላከል ኃይልና ችሎታ እንደለውም እንገነዘባለን፡፡ በመጨረሻም አቸናፊ እንደሚሆን ብዥታ አይኖረንም፡፡ ይህ ኃላፊነት የማይሰማው ጠባብ ብሔረተኛ ፥ አሸባሪና አጥፊ የወያኔ ቡድን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በእርሱ እንዲተላለቅ በጎሳና በኃይማኖት ከፋፍሎ እንዲተላለቅ ወደ ጦርነት አፋፍ እየገፋው ነው፡፡ ሕዝባችን ግን አሁንም ቢሆን፥ ከእርስ በእርስ ጦርነት ይልቅ፥ የሠላም ዋጋ እጅግ የከበረ መሆኑን ከልብ ያመንበታል፡፡ ይህ ዕምነቱ ግን ከፍርሃትና ከድክመት የመነጫ ሳይሆን፥ የወያኔን የአጥፍቶ መጥፋትን ተልዕኮ ለማከሽፍ ሲል ብቻ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በወያኔ ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት የሚደረገው ብልኅነትና አስተዋይነት፥ የታላቅነትና የአቸናፊነት ምልክት እንጅ የድክመትና የተቸናፊነት ምልክት አይደለም፡፡

በእርግጥም ሀገራችን ዛሬ ከምንም በላይ ሠላምና መረጋጋት ያስፈልጋታል፡፡ የጦርነት አባዜ ከሀገራቸን መወገድ አለበት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመከራና ከፍዳ አዙሪት መላቀቅ አለበት ብለን ከልብ እናምናለን፡፡ ይህ ሲባል፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ የዘረኞች አምባገነን ሥርዓት ለመላቀቅ በሚያደረገው የዴሞክራሲያዊ ትግል ማነኛውንም ስልትና ስትራተጅ ሁሉ ከመፈትሽ ሊነፈግ ይገባዋል ማለት አይደለም፡፡ ታዲያ በአሁኑ ወቅት፥ ብሔራዊ አቅጣጫችንና ራዕያችን ምን መሆን ይገባዋል? ተብሎ ሲጠየቅ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚከተሉትን ግንዛቤዎች ለመፈተሽ ምርጫ ይኖረዋል፡፡

1) ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሰላምና ህጋዊ ትግሉን በር ቢከረችመውም፥ አሁንም ቢሆን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የሠላሙን ትግል ወደ አርዕድ-አንቀጥቅጥ ኃይል ለመለውጥ የሚያስችለው ዕምቅ ኃይል አለኝ ብሎ ያምናል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ የሰላሙንና የዲፕሎማሲውን ትግል በአዲስ ስልትና ዘዴ አቀነባብሮ መታገል የተቃወሚው ኃይል ዓይነተኛ አጀንዳ ሊሆን የገባል፡፡ የዚህ ትግል ሂደት የመረቃ ውጤት ሊያስመዘግብ የሚችለው ግን ሁሉንም ባካተተና ባሳተፈ፥ቀጣይ ሂደት ነው፡፡ እስካሁን የተደረገው ጥረት የተቻለውን ሁሉ አላደረገም በይባለም፥ ተፈላጊውን ወጤት ግን አስመዝግቧል ማለት አይደለም፡፡ በግድ የተባበረ ኃይል አስፈላጊ መሆኑን ለማንም የሚሰወር አይደለም፡፡

2) ወያኔን ማንበርከክ የሚቻለው በሁሉንተናዊ መንገድና ዘርፈ- ብዙ በሆነ ትግል ለመሆኑ ማንም ኢትዮጵያዊ ከምንም ጊዜ በበለጠ አሁን ተረድቷታል፡፡ በድንቁርና ትዕቢት የተወጠሩትን የወያኔ መሪዎች ወደ ክብ ጠረጴዛ ለሰላም ውይይት እንዲመጡ ለማስገደድ፥ የተቃዋሚው ክፍል የፈረጠመ ጡንጃና የሚነክስ ጥርስ ያሸዋል ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወሰነ ቆይቷል

3) በአንድና ሁለት ተራ ቁጥሮች የተጠቀሱትን ነጥቦችን አቀንባብሮ ተግባራዊ ለማድረግና ውጤት ለማስመዝገብ ከተፈለገ፥ በብሔራዊ ደረጃ ሀገርን ማዳን የሚያስችል ሀገራዊ ማዕከል መፍጠሩ ይዋል ይደር የሚባል አይደለም። ከዚህ ሀገራዊ ማዕከል ሊመነጭ የሚችለው ደግሞ፥ ብሔራዊ አቅጣጫ ቀያሽ የትግል ስልትና ይህንንም በተግባር የሚተረጉም ሀገር አቀፍ ማዕከላዊ እዝ ቢሆን ይመረጣል። የብሔራዊ ትግል አቅጣጫ ከተነደፈ፥ ሁሉም የዜግነት ኃለፊነቱንና ግዴታውን ተገንዝቦ የየድርሻውን ሊያበረክት ይችላል። የኢትዮጵያን ሕዝብ በሞላ ያሳተፈ ሀገር አቀፍ ትግል ከተካሄ ደግሞ ለዲሞክራሲያዊ የሚደረገው ትግል ግቡን የማይመታበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም።

///////////////////------///////////////////////////